# የጠራ የወንጌል መልእክት

በዛክ ፑነን

በዚህ ገለጻ ‘ዳግመኛ መወለድ’ ወይም ‘ከኃጢያት መዳን’ ምን ማለት እንደሆነ ለማስረዳት እሞክራለሁ። ከኃጢያት ለመሸሽ የመጀመሪያው እርምጃ ንስሃ መግባት ነው። ስለዚህ ንስሃ ለመግባት ኃጢያት ምን እንደሆነ ማወቅ አለብን። በዘመናችን ስለኃጢያት ብዙ የተሳሳተ አመለካከት ስላለ ንስሃም በበርካታ ክርስትያኖች ዘንድ የተሳሳተ ትርጉም ተሰጥቶታል። በዘመናችን የክርስትና ደረጃ እጅግ በጣም ዝቅ ብሏል። ዛሬ በብዙ ሰባኪዎች የሚሰበከው ወንጌል ስለ እውነት በጣም የተበረዘ አመለካከት ያለው ነው። በአሁኑ ዘመን አብዛኛውን ጊዜ የሚሰበከው ሰዎች በእየሱስ እንዲያምኑ ብቻ ነው። ነገር ግን ሰዎች ንስሃ ካልገቡ በእየሱስ ማመን ብቻ  አያድንም።

ዳግመኛ መወለድ የክርስቲያን ህይወት መሠረቱ ነው።  ይህንን መሠረት ሳንጥል የቀና ህይወት ብቻ ብንኖር ክርስትናችን ከሌሎች ሃይማኖቶች የተለየ አይሆንም።  የዘመኑ የወንጌል ሰባኪዎች የሚያስተምሩት ሰዎች ጥሩ ህይወት እንዲኖሩ ብቻ ነው።  ነገር ግን ጥሩ ህይወት በመሠረት ላይ እንደሚገነባው ህንጻ ነው እንጂ መሠረቱ አይደለም።  ዋና መሠረቱ ዳግመኛ መወለድ ነው።  ሁላችንም ከዚያ መጀመር አለብን።

ስለ ዳግመኛ መወለድ እየሱስ በዮሐንስ 3:3 ላይ ከኒቆዲሞስ ጋር ሲነጋገር ጠቅሶታል። ኒቆዲሞስ የሃይማኖት መሪና እግዚአብሔርን የሚፈራ የቀና ህይወት የሚኖር ሰው ነበር። ሆኖም እየሱስ ሰው እንደገና  ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ እንደማይችል ነግሮታል።  ከዚህም የምንገነዘበው ምንም አይነት ጥሩ ሰዎች ብንሆን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ከመንፈስ መወለድ እንደሚያስፈልገን ነው። ከዚያም በተጨማሪ እየሱስ እራሱ ከፍ ብሎ እንደሚሰቀልና እንደሚሞት እንዲሁም በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የዘለዓለም ህይወትን እንደሚያገኙ ነግሮታል። (ዮሐንስ 3:14, 16)።

ቀጥሎም እየሱስ ሰዎች ስራቸው ክፉ ስለሆነ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን እንደወደዱና በእውነት የሚመላለሱ ግን ከኃጢያት ለመዳን ወደ ብርሃኑ  እንደሚመጡ ነግሮታል። ዳግመኛ ለመወለድ ወደ ብርሃኑ መምጣት አለብን።  ይህም ማለት ምንም ሳንደብቅ በእውነት ለእግዚአሔር ኃጢያታችንን መናዘዝ ነው።

የሰራነውን ኃጢያት ሁሉ ልናስታውስ እንደማንችል ግልፅ ነው።  ግን ኃጢያተኛ መሆናችንን አምነን መቀበልና የምናስታውሰውን ማንኛውንም ኃጢያት ለእግዚአብሔር መናዘዝ አለብን።  ኃጢያት በጣም ግዙፍ ነገር ነው።  እኛ ግን በመጀመሪያ በራሳችን ውስጥ የሚኖረውን ኃጢያት የምናየው በጣም ትንሹን ክፍል ነው።  ይህም በትልቅ አገር እየኖረ አካባቢውን ብቻ እንደሚያውቅ ሰው ሊመሰል ይችላል።  ነገር ግን ከተገለፀልን የኃጢያት መንገዳችን ስንመለስ ቀስ በቀስ ይኼን ግዙፍ የኃጢያት አገር በእኛው ህይወት ውስጥ እናየዋለን።  በዚህ  በተገለፀልን የብርሃን  መንገድ መመላለስ ስንጀምር ኃጢያታችንን በበለጠ ማየት እንችላለን።  ስለዚህ  ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በእውነት በመመላለስ እራሳችንን ከኃጢያት በበለጠ ማንጻት እንችላለን ማለት ነው።

ሌላ ምሳሌ በመጠቀም ለማስረዳት ልሞክር። ብዙ ቆሻሻ ክፍሎች ባለው ቤት ውስጥ

እየኖርን ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እንዲመጣና ከእኛ ጋር እንዲኖር እንፈጋለን እንበል። እርሱ ግን በቆሻሻ ክፍሎች ውስጥ መኖር ስለማይችል እያንዳንዱን ክፍል እንድናጸዳ ይረዳናል። ቀስ በቀስ ሁሉም ክፍሎች ይጸዳሉ። በክርስትና ህይወታችንም ውስጥ በቅድስ ና የምናድገው እንደዚህ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሁሉም ቦታና ለሁሉም ሰው አንድ አይነት መልእክት እንደሚሰብክ ተናግሯል። ይኼውም አንደኛው ንሰሃ በመግባት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ሲሆን ሁለተኛው በጌታ በእየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው (ሐዋ 20:20)። ጥሩ መሠረትን በህይወታችን ለመጣልና ዳግመኛ ለመወለድ እነዚህ ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው። እግዚአብሔር ንስሃን እና እምነትን አንድ ላይ አጣምሯቸዋል። ብዙ የክርስትያን ሰባኪዎች ግን እየለያዩዋቸው ነው።

በአሁኑ ዘመን እምነት በአብዛኞቹ የወንጌል ሰባኪዎች እየተሰበከ ሲሆን ንስሃ መግባት ግን ሳይጠቀስ ይታለፋል። ነገር ግን በእምነት ብቻ ዳግመኛ መወለድ አንችልም። ሴት ልጅ ብቻዋን ለመጸነስ እንደማትችል ሁሉ ወንድም ደግሞ ብቻውን ልጅ መውለድ አይችልም። የስጋዊ ልጅ ለመውለድ ወንድና ሴት አብረው መሆን እንዳለባቸው ሁሉ አዲስ የመንፈስን ልጅ በውስጣችን ለመውለድም ንስሃና እምነት መጣመር አለባቸው። ይህም ማለት አዲስ ልደት በመንፈሳችን ይከሰታል። ይህ መንፈሳዊ ልደት እንደ ስጋዊ ልደት ሁሉ በእርግጥና በቅጽበት ይፈጸማል እንጂ ቀስ በቀስ የሚከሰት ነገር አይደለም።

ለስጋዊው ልደት የመዘጋጃ ወራቶች እንዳሉት ሁሉ ምናልባት አዲሱ የመንፈሳዊ ህይውትም የመዘጋጃ ጊዜ ሊኖረው ይችላል። የመንፈሳዊ ልደት ግን እንደስጋዊ ልደት ሁሉ እውን የሚሆነው ወዲያው ነው። ሆኖም አንዳንድ ክርስትያኖች የአዲሱን ልደታቸውን ቀን በትክክል ላያውቁ ይችሉ ይሆናል። እኔም ብሆን የራሴን አዲስ ልደት ቀን አላውቅም። ይህም አንድ ሰው የስጋዊ ልደቱን ቀን እንደአለማወቅ ይመሰላል። ነገር ግን ያ ሰው በህይወት እስካለ ድረስ ይህ አሳሳቢ አይደለም። ዋናው ቁም ነገር አንድ ሰው በክርስቶስ ህይወት እንዳለው ማረጋገጡ ላይ ነው።

ወደ እግዚአብሔር የሚያመጣን መንገድ እየሱስ ብቻ ነው ስንል አእምሮ ጠባቦች እየሆንን ነውን? ይህን በምሳሌ ልመልስ ፥ አባቴን በእውን ወይም ፎቶውን አይቶ የማያውቅ ሰው አባቴ ምን እንደሚመስል ማወቅ አይችልም። በተመሳሳይ መንገድ እኛ እግዚእብሔርን አይተን ስለማናውቅ ስለ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ መንገዱ ምንም ማወቅ አንችልም።

እየሱስ ክርስቶስ ግን ከእግዚአብሔር የመጣ በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር የሚመራንን ትክክለኛ መንገድ ሊያሳየን የሚችል እርሱ ብቻ ነው። "መንገዱ እኔ ነኝ በእኔ ብኩል ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አብ የሚመጣ የለም" ብሏልና (ዮሐንስ 14:6)። እየሱስ ስለራሱ የሚገልጸውን ማለትም ወደ እግዚአብሔር አብ የሚወስደው ብቸኛ መንገድ መሆኑን ስናስብ የተናገረው በእርግጥ እውነት መሆኑን ካላመንን እርሱ ውሸታምና አታላይ ነበር ማለታችን ነው። ማንኛችን ነን ደፍረን እየሱስን ውሸታምና አታላይ ነበር ለማለት የምንችለው? እየሱስን ጥሩ ሰው ወይም ነብይ ነበር ማለትም አንችልም፤ ውሸታምና አታላይ ሰው ጥሩ ሰው አይደለምና ። ስለዚህ እየሱስ በእርግጥ በሰው አምሳያ የመጣው እግዚአብሔር እንደነበር በዚህ እናረጋግጣለን።

የእውነት መንገድ ሁሌ ጠባብ ናት። በሂሳብ 2+2 ሁልጊዜ 4 ነው። አእምሮአችንን አስፍተን 3ን፣ 5ን፣ ወይም 3.9999ን እንደ አማራጭ መልሶች መቀበል አንችልም።

እንደነዚህ  አይንቱን የተለያዩ መልሶችን እንደ እውነት ከተቀበልን የሂሳብ ድምራችን የተሳሳተ ይሆናል። ሌላ ምሳሌም ብንጠቀም ምድር ፀሃይን እንደምትዞር እናውቃለን። ግን አስተሳሰባችንን አስፍተን ፀሐይ ምድርን ትዞራለች የሚል አዲስ ዕንሰ ሃሳብን ብንቀበል ደግሞ የአስትሮኖሚ ትንተናችን የተሳሳተ ይሆናል። ውሃ በኬሚስትሪ የሁለት ንጥረ ነገሮች ማለትም የሃይድሮጅንና የኦክስጅን ጥምር $H_2O$ እንደሆነ የታወቀ ነው፤ አስተሳሰበ ሰፊ ሆነን ግን የውሃ ተፈጥሮን የያዘውን $H_2O$ ጨው ነው ብንል እንሳሳታለን። ስለዚህ እውነት በሁሉም ረድፍ ፍፁምና ጠባብ መሆኗን በዚህ እናያለን። የእግዚእብሔርም መንገድ እንዲሁ ነው። የሰፋ አስተያየት በሂሳብ በአስትሮኖሚና በኬሚስትሪ አደገኛ ስህተቶችን እንደሚያጣ ሁሉ ስለእግዚአብሔርም እውነት እንዲሁ ያሳስታል።

የሰው ፍጡር ሁሉ ኃጥያተኛ እንደሆነና እየሱስም ለኃጥያተኞች እንደሞተ መፅሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ስለዚህ ወደ እየሱስ በስመ ክርስቲያንነታችን ከመጣን እርሱ ኃጥያታችንን ይቅር አይለንም ለክርስትያኖች አልሞተምና ለኃጥያታተኞች እንጂ።  አንድ ሰው ይቅር የሚባለው "ኃጥያተኛው እኔ ነኝ" ብሎ ወደ እየሱስ ሲመጣ ብቻ ነው።

የማንኛውም ቤተ ክርስቲያን አባል መሆናችንም ይቅርታን ሊያሰጠን አይችልም። ምክንያቱም እርሱ የሞተው ለቤተክርስቲያን አባሎች ሳይሆን ለኃጥያተኞች ነውና። ስለዚህ ወደ እርሱ እንደ ኃጥያተኛ ከቀረብን ለኃጥያታችን ወዲያውኑ ይቅርታን እናገኛለን።

ሁላችንም ኃጥያተኞች እደሆንን ለማወቅ ቀላል ነው ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ህሊናን ለሁላችንም ሰጥቶናልና።  በተለይም ልጆች ጥሩውን ከመጥፎ በቶሎ መለየት የሚያስችላቸው ብሩህ ህሊና አላቸው።  እያደጉ ሲኼዱ ግን ያ ብሩህ ህሊና ጠንካራና ግድ የለሽ ሊሆን ይችላል።  የሶስት አመት ልጅ ውሸት ሲናገር ህሊናው ስለሚገስጸው ጥፋተኛነቱ ፊቱ ላይ ያስታውቃል።  ከአስራ አምስት አመት በኋላ ግን ይኼው ልጅ የሚገስጸውን የህሊና ድምጽ እየደጋገመ ችላ በማለት ውሸትን በድፍረት መናገር ይችላል። አዲስ የተወለደ የሕጻን የውስጥ እግር ከመለስለሱ የተነሳ በላባ እንኳን ቢዳስሱት ይሰማዋል።  የአዋቂ ተረከዝ ግን ከመጠንከሩ የተነሳ በኀይል ካልወጉት በስተቀር እንዲሁ በመርፌ ቢዳስሱት አይሰማውም።  ልጆችም ሲያድጉ ህሊናቸው እንዲሁ ይደነድናል።

ሕሊና አዋቂ መሆናችንን የሚነግረንና ጥሩና መጥፎን ለመለየት የሚያስችለን እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠው መሠረታዊ ድምጽ ነው።  ስለዚህ ድንቅ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። እየሱስም በሉቃስ 11:34 ሕሊናን የሰውነት መብራት ወይም የሰውነት አይን ነው ብሎታል። ይኼንን አይን ተጠንቅቀን ካልጠበቅን አንድ ቀን የመንፈሳዊ እውሮች እንሆናለን።  የሕሊናን ተግሳጽ ችላ ማለት ወደ አይናችን የሚገቡትን ጥቃቅን ብናኞች ችላ እንደማለት ነው። አንድ ቀን ፍጹም የመንፈሳዊ ዕውሮች እንሆናለን።

ህጻናት ሲወለዱ ሃይማኖት የላቸውም ሁሉም አንድ አይነት ናቸው።  ከሁለት አመት በኋላም ያው ናቸው ፥ ራስ ወዳድና ጠበኛ። ነገር ግን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ወላጆቻቸው በተለያየ እምነቶች ያንጿቸዋል።  የተለያየ ሃይማኖትም ይዘው የሚያድጉት በዚህ ምክንያት ነው።  ከ90%  በላይ የሚሆኑ የእምነት ተከታዮች የሚከተሉት ሃይማኖት ቤተሰቦቻቸው የመረጡላቸውን ነው።

እግዚአብሔር ግን ሁላችንንም እንደ ኃጥያተኞች እንጂ እንደ ተለያዩ የእምነት ተከታዮች አያየንም። እየሱስ ከሰማይ ወደ ምድር የመጣው ለዓለም ኃጥያተኞች ለመሞት ነው። እርሱ የመጣው ጻድቃን እንደሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ብቁ ነን ብለው ለሚያስቡት ሳይሆን ኃጥያተኛነታቸውን አምነው ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ የማይችሉ መሆናቸውን ለተቀበሉት ነው። ኃጥያተኞች እንደሆንን ህሊናችን ይነግረናል። ስለዚህ ለምንድን ነው ወደ እየሱስ ቀርበን "ጌታ ሆይ ኃጥያተኛና ስህተተኛ ነኝ" ማለት የሚያስቸግረን?

አንዳንድ ሰዎች 'እግዚአብሔር ጥሩ አምላክ ከሆነ እነደ አባት ኃጥያታችንን ሳይቆጥር ለምን ይቅር አይለንም?' ብለው ይጠይቁ ይሆናል። አንድ ልጅ በጣም ውድ እቃን ሰብሮ ቢጸጸትና አባቱን ይቅርታ ቢጠይቅ አባቱ ይቅር ይለዋል። እንደዚህ አይነቱ ስህተት ግን የሞራል ጉዳይ አይደለም። የኃጥያታችን ነገር እንደዚህ ምሳሌ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር በቅጽበት ይቅር ባለን ነበር። ኃጥያት ግን እቃን ሰብሮ እንደመፀፀት ቀላል ጉዳይ አይደለም። ኃጥያት ወንጀል ነው።

አንድ የፍርድ ቤት ዳኛ የራሱ ልጅ ተከሶ ከፊቱ ቢቀርብ ለልጁ 'ልጄ እወድሃለሁ ይቅር ብዬሃለሁ ስለዚህም አልቀጣህም' ማለት ይችላልን? ማንኛውም ፍትህን የማስከበር ፍላጐት ያለው ምድራዊ ዳኛ እንዲህ ያለውን ፍርድ በፍጹም አይፈርድም። በእርሱ አምሳያ ለተፈጠርን ሁሉ ደግሞ የፍትህ ስሜት የኃያሉ እግዚአብሔርን ፍጹም ፍርድ በመጠኑ ያንፀባርቃል። ስለዚህ ከባድ ጥፋት ስናጠፋእግዚአብሔር እንደ ፈራጅነቱ 'በጣም እወዳችኋለሁ ነገር ግን ወንጀልን ፈጽማችኋል ለእርሱም እቀጣችኋለሁ' ማለት አለበት። እዚያ ፍርድ ቤት ውስጥ የዳኛው ልጅ ስለወንጀሉ ምንም ያህል ቢጸጸት አባቱ አሁንም እንደዳኝነቱ ልጁን መቅጣት አለበት። ለምሳሌ ልጁ ባንክን በመዝረፍ ቢወነጀል አባት ልጁን ሕጉ በወሰነው መሠረት ሙሉ ቅጣቱን ይቀጣዋል ፥ እንበል አንድ ሚሊዮን ብር።

ልጁ ቅጣቱን ለመክፈል ይኼን ያህል ገንዘብ ስለማይኖረው ወደ እስር ቤት መኼድ አለበት። አባትየው ግን ካባውን አውልቆ ከፍርድ ወንበሩ ላይ ይነሳና በህይወቱ ሙሉ ያጠራቀመውን የግል ገንዘብ አውጥቶ አንድ ሚሊዮን ብር ለቅጣቱ እንዲከፍል ለልጁ ይሰጠዋል። ታዲያ ይኼ ልጅ አባቱን 'አልወደድከኝም' ብሎ ሊወንጅለው ይችላልን? የለም፤ በተጨማሪም ማንም ሰው ትክክለኛ ዳኛ ስላለመሆኑ ሊወነጅለው አይችልም። ምክንያቱም ለልጁ በሕጉ መሠረት የሚገባውን ቅጣት ሰጥቷልና። እግዚአብሔር ለኛምያደረገልን ልክ እንደዚህ ነው። እንደ ዳኝነቱ ሁላችንም ለኃጥያታችን መሞት እንዳለብን አወጀ። ከዚያም በሰው አምሳል ወደ ምድር ወርዶ ያንን ቅጣት እራሱ ተቀበለ።

መፀሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን እግዚአብሔር አንድ ቢሆንም ሶስት አካል እንዳለው ነው ፥ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ። እግዚአብሔር አንድ ብቻ ቢሆን የሰማይ ዙፋኑን ለቆ ወደ ምድር እንደ ሰው በእየሱስ ሰውነት በፍፁም ሊመጣ አይችልም ነበር። አለበለዚያ ዓለምን ማን ያስተዳድራት ነበር? ነገር ግን እግዚአብሔር በሶስት አካል ስለሚኖር ወልድ አምላክ ወደ ምድር መጥቶ ለእኛ ኃጥያት የዓለም ዳኛ በሆነው በአብ አባቱ ፊት ለመሞት ቻለ። አንዳንድ ክርስትያኖች እግዚአብሔር በአንድ አካል ብቻ እንደሚኖር ስለሚያምኑ እርሱም በእየሱስ ፥ሰዎችን በእየሱስ ስም ብቻ ያጠምቃሉ።

ይህም አደገኛ ስህተት ነው፡ 1ኛ ዮሐንስ 2:22 ማንም አብንና ወልድን የሚክድ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ እንዳለበት ይነግረናል። ምክንያቱም ወልድ አምላክ በሰው አምሳያ እንደ እየሱስ ክርስቶስ የራሱን ፈቃድ ትቶ የአባቱን ፈቃድ ሊፈጽምና የኃጥያታችንን ቅጣት በአብ በአባቱ ፊት ሊሸከም መምጣቱን ይክዳሉ (1ኛ ዮሐንስ 4:2,3)።

እየሱስ ወደ አለም ሲመጣ ሙሉ እግዚአብሔርና ሙሉ ሰው ነበር። እርሱ በመስቀሉ ላይ ሲሞት የዓለምን የኃጥያት ቅጣት ወሰደ። የኃጥያታችን ቅጣት ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ስለዚህ እየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ ከሰማይ አባቱ ተለይቶ ነበር። እንደዚህ ያለውን መለየት ማንም ሰው ሊቋቋመው የማይችል እጅግ የከፋ ስቃይ ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር የተወው ስፍራ ገሃነም ብቻ ነው። እግዚአብሔር በዚያ ስለሌለ ገሃነም የሰይጣን ክፋት ሙሉ በሙሉ የሚከሰትበት ቦታ ነው። ገሃነምንም አሰቃቂ የሚያደርገው ይኼው ልክ የሌለው ክፋት ነው። እየሱስም በመስቀል ላይ እያለ የተቀበለው ይኼንን ቅጣት ነው። እርሱ ለስድስት ሰዓታት በተሰቀለበት ጊዜ ለመጨረሻው ሶስት ሰዓቶች እግዚአብሔር ትቶት ነበር። ፀሐይ ጨለመች መሬትም ተንቀጠቀጠች እየሱስም ከአባቱ ጋር ያለው ግንኙነት ለሶስት ሰዓታት ተቋረጠ። አብ የክርስቶስ ራስ እንደመሆኑ (1ኛ ቆሮንጦስ 11:3) አባቱ እየሱስን ሲተወው የእየሱስ ስቃይ አንገቱን የመታረድ ያህል ነበር። የኛ አዕምሮ የደረሰበት ስቃይ ምን ያህል እንደነበረ ሊገነዘብ አይችልም።

እየሱስ ተራ ፍጡር ብቻ ቢሆን ኖሮ ከአዳም ጀምሮ ለኖሩ ህዝቦች ቅጣትን በፍፁም መሸከም አይችልም ነበር። ምክንያቱም አንድ ፍጡር በቢሊዮን በሚቆጠሩ ነፍሰ ገዳዮች ምትክ ሊሰቀል አይችልምና። ነገር ግን እየሱስ ዘላለማዊ አምላክ በመሆኑ ይህንን ቅጣት ሊሸከም ችሏል።

ዘላለማዊም ስለሆነ በሶስት ሰዓት ውስጥ ዘላለማዊ ቅጣትን ለመሸከም ቻለ።

እየሱስ ክርስቶስ አምላክ ባይሆንና እግዚአብሔር አብ ለእኛ ኃጥያት ቀጥቶት ቢሆን ኖሮ ይህ ታላቅ የፍትህ መዛባት ይሆን ነበር። ምንም እንኳን ሌላው ሰው ቅጣቱን ለመውሰድ ቢፈቅድም እግዚአብሔር ባንዱ ወንጀል ሌላውን ሊቀጣ አይችልም። ለምሳሌ ጓደኛችን የእኛን ቅጣት ወስዶ በእኛ ቦታ መሰቀል አይችልም። ይህ ፍትህን ያዛባታል። እየሱስም ለእኛ ኃጥያት የተቀጣው እንደ ሰው ፍጡር ብቻ ቢሆን ኖሮ ይኼን ታላቅ የተዛባ ፍርድ ያደርገው ነበር።

ስለዚህ ማንኛውም ፍጡር የኃጥያታችንን ቅጣት ለመሸከም በፍፁም እንደማይችል ግልፅ ነው። ያንን ቅጣት ለመውሰድ የሚችል የፍጥረታት ዳኛ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ እኛን ለመቅጣት መብት እንዳለው እንዲሁም ቅጣታችንን እራሱ ለመሸከም መብት አለው። እየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም ሲመጣ ያደረገው ይኼንን ነው። የክርስትና ሃይማኖትም የተመሠረተው በነዚህ ሁለት ታላላቅ እውነታዎች ነው ÷ የመጀመሪያው ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጥያት መሞቱ ሲሆን ሌላው በሶስተኛው ቀን ከሞት መነሳቱ ነው።

ክርስቶስ ከሞት ባይነሳ ኖሮ እሱ እግዚአብሔር ስለመሆኑ ማስረጃ አይኖርም ነበር። የሱ ከሞት መነሣት እርሱ ያለው ሁሉ እውነት ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ለዓለም ኃጥያት እሞታለሁ ያለ ማንም የሃይማኖት መሪ እንደሌለ ሁሉ ከሞት የተነሣም የሃይማኖት መሪ የለም። እነዚህ ሁለት እውነታዎች እየሱስ ክርስቶስን ልዩ ያደርጉታል።

ሁሉም የዓለም ሃይማኖቶች ለሌሎች ጥሩ እንድናደርግ ያስተምሩ ይሆናል። የክርስትና ሃይማኖት ግን ልዩ መሠረት አለው። ይኸውም ክርስቶስ ለኃጥያታችን መሞቱና ከሞትም መነሣቱ ናቸው። እነዚህን ሁለት እውነታዎች ከክርስትና ብናወጣቸው ክርስትና እንደሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ይሆናል።

ሁላችንም የተፈጠርነው ለእግዚአብሔር ቢሆንም ሁላችንም ለራሳችን ኖረናል። ስለዚህ ወደ እግዚአሔር ስንቀርብ የእግዚእብሔር የሆነውን ንብረት ለብዙ አመታት ሰርቀው እንደተፀፀቱ ሌቦች መሆን አለብን። ወደ እርሱ ስንመጣ ክርስቶስን በማመስገን፣ ለኃጥያታችን መሞቱንና መነሣቱን ዛሬም ህያው መሆኑን በማመን ነው።እየሱስ ህያው ባይሆን ኖሮ ዛሬ ለእሱ መፀለይ አንችልም ነበር። የሞተን ሰው ማናገር አይቻልምና። ነገር ግን እየሱስ ከሞት ስለተነሣ ከእርሱ ጋር መነጋገር እንችላለን።

ክርስቶስ ከሞት ከተነሣና ካረገ በኋላ የሥላሴዎች ሶስተኛ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር መጥቷል። መንፈስ ቅዱስ እንደ እየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አካል ነው። ወደ ምድርም የመጣው ህይወታችንን በእሱ እንዲሞላን ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ካስገዛን ቅዱስ ሊያደርገን ይችላል። በመንፈስ ቅዱስም ስንሞላ ከኃጥያት ነጻ የሆነ ኑሮ እንድንኖር ያስችለናል። መንፈስ ቅዱስ በጴንጠ ቆስጤ ዕለት ባይወርድ ኖሮ ማንም ሰው እንዲህ አይነቱን ህይወት ሊኖር አይችልም ነበር። ከዚያ በፊት ሰዎች በህይወታቸው ማሻሻል የሚችሉት ለሰው የሚታየውን ውጫዊ ተግባራቸውን ብቻ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ግን እግዚአብሔር እራሱ በውስጣችን ስለሚኖር የሱን ህይወት እንድንኖር ያስችለናል።

የወንጌልም ድንቅ መልእክት እግዚአብሔር ይቅር ሲለን ልባችን በፍፁም ንፁህ እንደሚሆንና ክርስቶስም በመንፈስ በውስጣችን እየኖረ ሰውነታችንን የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደሚያደርገው ነው።

አንድ ጊዜ ሲጋራ ከሚያጨስ ክርስቲያን ጋር ስነጋገር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያጨስ እንደሆነ ጠየቅሁት። እርሱም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነ በዛ ውስጥ ማጨስን እንደማያስብ ነገረኝ። እኔም የእግዚአብሔር ማደሪያው የሱ ሰውነት እንጂ የቤተ ክርስቲያን ህንጻው እንዳልሆነ ነገርኩት። ክርስቶስ በውስጣችን ሲኖር ሰውነታችንን የእግዚአብሄር ማደሪያ ስለሚያደርገው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማመንዘርና አጸያፊ መፅሔቶችን ማየት እንደሚያስፈራን ሁሉ በሰውነት አካላችንም የምናደርገውን መጠንቀቅ አለብን። የማጨስ፣ የመጠጣት፣ ዕፅ በለሶችን የመውሰድ ሱስና የተበላሹ ሃሳቦችን አእምሮአችን እንዲያስብ መፍቀድ ቀስ በቀስ ሰውነታችንን ብቻ ሳይሆን አእምሮአችንንም ያጠፉዋል።

የክርስትና ህይወት እንደ ሩጫ ወድድር ሊመሰል ይችላል ፥ የሩጫው መጀመሪያ መስመር ከኃጥያት ተመልሰን ዳግመኛ ስንወለድ ነው። ከዚያም እስከ እድሚያችን መጨረሻድረስ የምንሮጠው የማራቶን ውድድር እንጀምራለን ፥ በየቀኑ በመሮጥም ቀስ በቀስ ወደ መጨረሻው መስመር እንጠጋለን ሩጫውን ግን ማቆም የለብንም።

ሌላ ምሳሌ ለመጠቀም ፥ ዳግመኛ ስንወለድ የቤታችንን መሠረት እንጥላለን። ከዚያ በኋላ ብዙ ፎቆች ያሉትን ህንጻ ቀስ በቀስ መገንባት እንጀምራለን። በእንደዚህ አይነት ጥሩ

አኗኗር ቀስ በቀስ መጥፎ የሆነውን ሁሉ ከህይወታችን እያስወገድን በየጊዜው አምላካችንን እየመሰልን እንኼዳለን።

እንግዲህ ዳግመኛ ለመወለድ ምን ማድረግ አለባችሁ?

በመጀመሪያ ኃጥያታችሁን እመኑ።እራሳችሁን ከሌላ ሰው ጋር እያወዳደራችሁ በሃሳባችሁ ከነሱ የተሻላችሁ እየመሰላችሁ አትኩራሩ። ኃጥያት እጅግ አደገኛ መርዝ ስለሆነ ከመርዙ አንድም ሆነ መቶ ጠብታ ብትወስዱ መሞታችሁ አይቀርም። ስለዚህ የክርስትና ህይወታችሁን በጥሩ መንገድ መጀመር ከፈለጋችሁ ከመጨረሻው ኃጥያተኛ የማትሻሉ መሆናችሁን አምናችሁ መቀበል አለባችሁ።

ቀጥሎም በክርስቶስ እመኑ፥ ይኼም ማለት እራሳችሁን ለክርስቶስ ስጡ እንጂ በአእምሮአችሁ ብቻ ስለእርሱ ማንነት እመኑ ማለት አይደለም። ራሳችንን ሳንሰጥ አንድን ሰው ማመን እንችላለን። አንዲት ሙሽሪት በሰርጓ ቀን የምትጠየቀው ለሙሽህራው ራሷን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኗን ነው። እርሷ ግን 'ሙሽራው ጥሩ ሰው እንደሆነ አምናለሁ ግን ራሴን ለእርሱ ለመስጠትና ህይወቴን በሙሉ ከሱ ጋር ለማሳለፍ እርግጠኛ አይደለሁም' ብላ ብትመልስ በሙሽራው ላይ እምነት ስለሌላት ልታገባው አትችልም። ሴት ልጅ ስታገባ የህይወቷ አቅጣጫ በሙሉ ይለወጣል። በአንዳንድ ባህሎች ስሟን ጭምር ቀይራ የባሏን ቤተሰቦች ስም ትወስዳለች። በባሏ እምነት ስላላት ወዴት እንደሚወስዳት ባታውቅም የወደፊት ህይወቷን በሱ ላይ ተማምና ትተዋለች። በክርስቶስ ማመንም ይኼንን ይመስላል።

ክርስትና ቃሉን በአክብሮት ለመጠቀም ወ/ሮ ክርስቶስ እንደማለት ነው። በአንዳንድ ባህሎች አንዲት ሙሽራ የባልዋን ስም የራሷ የምታደርገው ባልዋን ካገባችው በኋላ ነው። እናንተም የክርስቶስን ስም ወስዳችሁ እራሳችሁን ክርስቲያን ብላችሁ መጥራት የምትችሉት እሱን ካገባችሁት ማለትም ራሳችሁን ለእሱ ፈጽሞ ከሰጣችሁ በኋላ ነው። አንዲት ሴት ሳታገባኝ የኔን ስም ወስዳ እራሷን ወ/ሮ ዛክ ፑነን ብላ ብትጠራ ትዋሻለች። እንዲሁም ማንም ራሱን ለክርስቶስ ፈጽሞ ሳይሰጥ እራሱን ክርስቲያን ብሎ የሚጠራም ሰው ይዋሻል።

ጋብቻ የዘለዓለም ትስስር ነው እንጂ ለጥቂት ቀናት አይደለም። ክርስትናም እንዲሁ የእድሜ ዘላለም መጣመር ነው። አንዲት ሴት ስታገባ በህይወቷ ሁሉ ላለመሳሳት ቃል እንደማትገባ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ስንጣመርም ፍፁም መሆን አለብን ማለት አይደለም። ያቺ ሴት ብዙ ጊዜ ትሳሳታለች ባሏም ብዙ ጊዜ ይቅር ይላታል። የሷ ቃል ኪዳን ግን ከባሏ ጋር እስከመጨረሻው ለመኖር ነው። ከክርስቶስ ጋር ያለን አንድነትም ይኼን ይመስላል።

የሚቀጥለው ደረጃ በውሃ መጠመቅ ነው። ጥምቀት የጋብቻን የምስክር ወረቀት እንድማግኘት ሊመሰል ይችላል። የጋብቻ የምስክር ወረቀት በማግኘት ብቻ መጋባት እንደማንችል ሁሉ በመጠመቅ ብቻም ክርስቲያን መሆን አንችልም። የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሚገኘው ከተጋባን በኋላ እስከሆነ ድረስ መጠመቅም የምንችለው ራሳችንን ለክርስቶስ ከሰጠን በኋላ ነው። የቀድሞ ህይወታችንን ትተን ክርስቶስን የህይወታችን ጌታ እንዳደረግነው የምንመሰክረው በጥምቀት ነው።

ጥሩ ባልና ሚስቶች እርስ በርሳቸው ብዙ እንደሚወያዩ ሁሉ እናንተም ክርስቶስን ማነጋገርና እሱም በመፀሐፍ ቅዱስ የሚነገራችሁን በየቀኑ ማዳመጥ አለባችሁ።

ጥሩ ሚስት ሁሉንም ነገር ከባሏ ጋር በመስማማት ታደርጋለች እንጂ ባሏን የማያስደስት ነገር በፍፁም አታደርግም። እውነተኛ ክርስቲያንም ክርስቶስን የሚያስቀይም ምንም ነገር አያደርግም። ከንቱ ነገሮችን ከማየት አይኖቹን እየመለሰ ከክርስቶስ ጋር ማድረግ የማይችለውን ማንኛውንም ነገር ብቻውን አያደርገውም።

ዳግመኛ እንደተወለድን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን? ሮሜ 8:16 ዳግመኛ ስንወለድ የእግዚአብሔር ልጆች መሆችንን መንፈስ ቅዱስ እራሱ ከመንፈሳችን ጋር እንደሚመሰክር ይነግረናል።

ማንም ሊያገኘው ከማይችል ጥሩ ጓደኛ ጋር ስለምንኖር እንዲህ አይነቱ ህይወት ድንቅ ህይወት ነው። እየሱስ ሁልጊዜ በሁሉ ቦታ ከእኛ ጋር ስላለ መቼም ብቸኛ አንሆንም። ችግራችንን ለእርሱ አዋይተን እንዲረዳንና መፍትሄ እንዲሰጠን መጠየቅ እንችላለን። እየሱስ የወደፊት ኑሮዋችንን በእጁ ስለያዘው ህይወታችን በደስታ የተሞላና ከሃሳብና ከፍርሃትም ነፃ ይሆናል።

ዳግመኛ መወለድ ከፈለጋችሁ ከልባችሁ ሆናችሁ እንዲህ ብላችሁ ፀልዩ፤

'ጌታ እየሱስ የእግዚአብሕር ልጅ እንደሆንክ አምናለሁ። ገሃነም የሚገባኝ ኃጥያተኛ ብሆንም ስለወደድከኝና ስለኃጥያቴ በመስቀል ስለሞትክልኝ አመሰግንሃለሁ። ከሞት ተነስተህ ዛሬም ህያው እንደሆንክ አምናለሁ። በኃጥያት ከተሞላ ህይወቴ ለመመለስ እፈልጋለሁ። እባክህ ኃጥያቴን ይቅር ብለህ ኃጥያትን የሚጠላ ልብ ስጠኝ። በማናቸውም ምክንያት የበደሉኝን ሁሉ ይቅር ብያለሁ። ጌታ እየሱስ በህይወቴ ውስጥ መጥተህ የህይወቴ ጌታ ሆነህ አሁኑኑ የእግዚአብሔር ልጅ አድርገኝ'።

የእግዚአብሔር ቃል 'ለተቀበሉት ሁሉ፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው' ይላል (ዮሐ 1:12)። ጌታ እየሱስም 'ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጪ አላወጣውም' ይላል (ዮሐ 6:37)።

ስለዚህ እርሱ እንደተቀበላችሁ እርግጠኛ ልትሆኑ ትችላላችሁ።

ከዚያም እርሱን 'ጌታ እየሱስ ኃጥያቴን ይቅር ብለህ ስለተቀበልከኝ ተመስገን። እባክህ በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝና ላንተ እንድኖር ኃይል ስጠኝ። ከዛሬ ጀምሮ አንተን ብቻ ማስደሰት እፈጋለሁ' እያላችሁ ለምኑት።

ካሁን በኋላም የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ እያነበባችሁ ጌታ በመንፈስ ቅዱሱ በየቀኑ እንዲሞላችሁ ጠይቁት። ከሌሎች ዳግመኛ ከተወለዱ ክርስቲያኖችም ጋር እየተገናኛችሁ አንድነትን ፍጠሩ። በክርስትና ህይወታችሁ ጌታን ለመከተል የሚያስችላችሁን ኃይል የምታገኙት እንደዚህ ብቻ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ወደ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን እንዲመራችሁ ለምኑት።

እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ።